# የሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም አዲስ እና

# ተደጋጋሚ ጭካኔ እና ቅጥፈት፤

በዚህ ዓመት በ 2017 በሚያዝያ ወር ፤ ዶክተር ስንታየሁ ካሣ በዳላስ የቴካሳስ ነዋሪ የሆነች፤ ስለ አባትዋ ኮሎኔል ካሣ ገብረማርያም፤የቤተሰብ ፍቅር፤ ሀገር ወዳድነት፤ ጀግንነት፤ ለሀገር መስዋዕትነተና እና ስለ ተፈፀመባቸው የአመራር ሴራና ተንኮል ጭምር የጻፈችውን የጀግና ሰው ታሪክ፤ መጽሐፉ ገበያ ወጥቶ አንብበናል ;;

ይህ መጽሐፍ የአባትዋን ለሀገር ታማኝነት የከፈሉትን ውለታ መግለጽዋ ብቻ ሳይሆን፤ ለመላው አንባቢ ትምህርት እንዲሆን የጀግኖችን መስዋዕትነት ሲያሳየን ፤ በአመራር አሻጥር ብዙ ጀግኖች ህይ ወታቸውን እንዳጡም ያስገነዝበናል፡፡

ኮሎኔል ካሣ ገበረማሪያም በአመራር ተንኮል፤ ረዳት በማሳጣት ፤ ስንቅና ትጥቅ በመከልከል በኤርትራ በረሃ ጠላት እንደከበባቸውና እጃቸውን ላለመስጠት ሀገሪቱንና የጦር ሃይሉን ላለማዋረድ ሲሉ በክብር እራሳቸውን በራሳቸው በችጉጥ ጥይት እንዲገድሉ ተገደዋል። የአፄ ቴዎድሮስን ጀግንነትና ምሳሌ ተላብሰው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል፡፡

ይህ አሳዛኝ ድርጊት እንዴት ሊደርስ ቻለ? ለምን? ዶክተር ስንታየሁ ካሣ ይህን መጽሐፍ ለመጻፍ ከአንድ መቶ ሰው በላይ እንዳነጋገረችና ረጂም አመታት እንደፈጀባት በመጽሐፉ ውስጥ ይነበባል።

ኮሎኔል ካሣ ገብረማርያም የገነት ጦር ት/ቤት 14 ኛ ኮርስ መሆናቸውና ፤ ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማ ርያም የዚሁ ት/ቤት 19 ኛ ኮርስ መሆኑ ይታውሳል። ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ በእውቀተና በሥልጣን የሚበልጡትን የፈራል። አብዮቱን ምክንያት እያደረገ ብዙ መኮንኖችን ፈጅቷል።
ብዙዎች እንደሚያውቁት ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማሪያም ሥልጣን ከመጨበጡ በፊት ፤አያሌ የቀድሞ ባለስልጣናትን ካስገደለ በኋላ ፤ ሌ/ኮሎኔል ኃይሉ ረጋሣ የተባለ ጉዋደኛውና አበልጁን በአብዮቱ ወቅት የልዩ አቤዮታዊ ጦር ፍርድ ቤት ዳኛ የነበረ፤ አብዮታዊ ወቅት በመሆኑ እሱና ጓደኞቹ የቀድሞው የኦሮሞ ስርዓት ይመለስ በሚል ጥያቄ አቅርበው ተሰወሩ ። በዚህ ጊዜ ደርግ ሽማግሌ ልከው ከተሰወረበት ምህረትና እርቅ ተደርጎልሀል ተብሎ እጁን እንደሰጠ ወዲያውኑ እሱንና ሌሎችን የኦሮሞ ነፃ አውጭ መሪ ናችሁ በማለት ያለፍርድ እስር ቤት ውስጥ በ 1967 በኢትዮጵያ ዘመን አቆ ጣጠር በጥይት ገደሏቸው።ከተገደሉት ውስጥ ጀኔራል ታደሰ ብሩ ይገኙበታል ። ሻለቃ ሲሳይ ሃብቴ ከአየር ኃይል የደርግ አባል ; ንቁና ምሁር በመሆኑ የአሜሪካ የ C I A አባል ነው በማለት ያለ ፍርድ በጥይት ተገደለ። ፒ ቲ ኦፊሠር ሚካኤል አስገዶም ከባህር ኃይል የደርግ አባል የነበረ ፤ደርግ የሚያደርገውን ግድያዎች፤ በተለይ ሌ/ኮሎኔል ዳንኤል የሚያደርገውን ጭፍጨፋና በሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ፈቃድና አመራር የዶክተር ሰናይ ልኬ የህዝብ አደራጅ ጽ/ ቤት ልዩ ጓድ የተባሉትን አፋኞች በመጠቀም ይፈጸም የነበረውን ግፍና ጭካኔ በገልጽ ይቃወም ስለ ነበረ ፤ አሥመራ በሥራ መልክ ልከውት ፤ አብሮት ከአዲስ አበባ በሚስጢር በተላከ ወታደር በ1968 እንደኢትዮጵያ አቆጣጠር አስገደሉት ። ገዳዩ ወታደር ሹመትና የገንዘብ ጉርሻ ተሰጥቶታል። በወቅቱ ይህ ግፍ በምርመራ ስተደረሰበት ፤ ጉዳዩ ን የሚከታተሉትን የደርግ አባላትና ለሥልጣኑ የሚቀናቀኑትን ሌሎቹንም የደርግ አባላት ጨምሮ 1/ ጀኔራል ተፈሪ በንቲ 2/ ሻምበል ዓለማየሁ ኃይሌ 3/ ሻምበል ሞገስ 4/ ሌ/ኮሎኔል አሥራት 5/ ሌ/ኮሎኔል ሕሩይ 6/ ሻምበል ተፈራ 7/ ፲ አለቃ ኃይሉ FEB. 3 1977 ( 1969 በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር _) በሙሉ በድንገት ረሸናቸው። በውጭም ብዙ መኮንኖችና ወታደሮች ተረሸኑ። ሌሎችም ለብዙ ዓመታት ታሠሩ። በዚያኑ ዓመተ ምሕረት 1969 በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ለማሳረጊያ በመጨረሻ የገደለው የደርግን ዋና መስራችና ተቀናቃኙን ሌ/ኮሎኔል አጥናፉ አባተን ነበር ። ሌ/ኮሎኔል አጥናፉም ቢሆ ን ንጉሡንና የቀድሞ ባለስልጣናትን ያስገደለ ስለሆነ ያገኘው የእጁን ነው ። ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ከማጣሪያ ግድያው በኋላ ርእሰ ብሔርና ሙሉ ፈላጭ ቆራጭ አምባ ገነን ሆነ። የገደላቸውና ያስገደላቸው በጣም ብዙዎች ስለሆኑ ለታሪክ ከመተው በስተቀር ዘርዝሮ ማቅረብ ያሳምማል።

ዶክተር ስንታየሁ ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያምን ለብዙ ሰዓታት አነጋግራለች። ጥያቄና መልሱ በመጽሐፉ ውስጥ ይገኛል። በመጽሐፉ በገጽ 379 ዶክተር ስንታየሁ ለሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ያቀረበችው ጥያቄ " ________ይሄ ሊከብድዎት ይችላል_===========ኮሎኔል ካሣን ይፈሯቸው ስለነበረ ። አውቀው ነው ወደዛ እንዲሄዱ ያደረጉት ይባላል። " በማለት ጠይቃለች። በተጨማሪም አባትዋ ለምን ያለበቂ ጥናት እንደተላኩ፤ ሌሎች መላክ ሲገባቸው ለምን ተለይተው አባትዋ ሊወጣ ወደማይችለው ውጊያ ሆን ተብሎ ተላኩ የሚልም ጥያቄ አቅርባለች።

ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ሁሉንም ክዷል። መካድ ብቻ አይደለም። እንደሚታወቀው ቀደም ሲል እንደሚያደርጉት ሁሉ ማለትም ኢሕአፓን ከመኤሶን፤ መኤሶንን ከወዝ ሊግ፤ ኢጭአትን ከሰደድ እያጋጩና እያገለሉ ኖረዋል። በወታደሩም በኩል የአካዳሚውን ምሩቅ ከሆለታ ገነት ምሩቅ ጋር ነባሩን ወታደር ከአዲሱ ወታደር ጋር፤ ጦር ሠራዊቱን ከፖሊሱ ጋር እያጣላ

ዘመኑን አራዝሟል። አሁንም በስደት ላይ እያለም የተፈጥሮ ውሸት ስለሚያጠቃው በኮሎኔል ካሣ ገብረማርያም መጽሐፍ በገጽ 381 ለቀረበለት ጥያቄ ብዙ የተወሳሰበ መልስ ከሰጠ በኋላ ፤መውጫ ሲጠፋው ለኮሎኔል ካሣ ገብረማርያም ሞትና ለሌሎችም የጦር ሠራዊት መኮንኖች ሞት ሁሉ የክብር ዘበኛ መኮንኖች ናቸው በማለት ከለመደ አፉ ወጥቷል። የሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ሽፍጥ በገጽ 381 " ________ምናልባት በዚያን ጊዜ እነ መርዕድና እነ ኃይለጊዎርጊስ ( ሁለቱም የክብር ዘበኛ ጀነራሎች ናቸው) እዛ ዘመቻ ምክር ቤት ውስጥ እያሉ እድሉ ገጥሟቸው እነ ካሣን በጣም አደገኛ ቦታ ሰደዋቸው ይሆናል። " በማለት የእነ ኮሎኔል ካሣን ስቃይ የወታደሮቹን እልቂት በክቡር ዘበኛ መኮንኖች ላይ ለጥፏል። እንደ እውነቱ ከሆነ በዘመቻው ምክር ቤት ውስጥ የነበሩት አብዛኛዎቹ መኮንኖች ከጦር ሠራዊት ነበሩ። ከዚህም ሌላ አሁን ያመካኘባቸውና የካዳቸው የክብር ዝበኛ መኮንኖች፤ በአንድ ወቅት የቅርብ ወዳጆቹና የጀነራልነት ማእረግ የሾማቸው ሰዎች ነበሩ።

አዎ ምን ይደረግ ከድሃይቱ ኢትዮጵያ የዘረፈውን ብዙ ሚልዮን ብሮች በመጠቀም በዚምባዌ ሀረሬ ከተማ ይንሸራሸራል። ዘርን በማጥፋት እና ወጣቱን ትውልድ በማኮላሸት ወንጀል ተከሶ ለፍርድ መቀረብ ሲገባው ፤ አሁንም እንድገና በሥልጣን ላይ እያለ ያጠፋው አንሶት የሞቱ ሰዎችንና ዘመዶቻቸውን ይቦጫጭቃቸዋል።

በዚሁ በ " ካሣ ገብረማርያም " መጽሐፍ በገጽ 381 ዶር ስንታየሁ ካሣ አሁንም ለሌ ኮሎኔል መንግሥቱ ከዚህ የሚከተለውን ትጠይቃለች " ____________አባቴ _ከጀኔራል አማን ሚካኤል ዓንዶም ጋር በጣም ቅርርብ ነበራቸው፤ ያክብሯቸውም ነበር።( ከተገደሉ በኋላ) በዚህ ምክንያት ያባቴ ስልክ ተጠልፎ ነበር እና የሚያስታውሱት ካለ ።" ብላ ለጠየቀችው ጥያቄ፤ ዋናውን ጉዳይ ሽፋፍኖ በ ጀኔራል አማን አንዶም ላይ ቅሬታ ማሰማት ቀጠለ። ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ስለ ጀኔራል አማን እንዲህ ይላል በገጽ 384 " __________ከዚያ በኋላ ( ከአሥመራ ከተመለሱ በኋላ ) ምንም ያደረጉት ነገር የለም ። እንዲያውም የሠሩት ሌላ ታሪክ ነው። ጀነራል ጎይቶም የሚባለው የኤርትራ ፈጥኖ ደራሽ ሠራዊት እሳቸው ጋ እራት ምሳ እየበላ ሰንብቶ እሳቸው ወደ አዲስ አበባ ሲመጡ ያለውን ጦር ይዞ ወደ ሻእቢያ ገባ። እና ሌላም ሌላም ነገር_____________" ከላይ ያነበብነው የሌ/ኮሎኔል አመላለስ በጣም የሚያሳዝን ውሸት ነው። ጀኔራል አማን ኤርትራን ሲጎበኙ ኤርትራ ነበርኩ። ጉብኝታቸውና በአሄዱበት ቦታ ያደረጉዋቸው ንግሮች ስለ አንድነትና ጸጥታ ስፈላጊነት ነው ። እዚህ ላይ አንድ እውነት ልግለጽ። ደርግ ከመፈጠሩ በፊት፤ የኢትዮጵያ ህዝብ አንድ እና የካርታ አቀማመጡም አንድ ያልተከፋፈለች ኢትዮጵያ ነበረች። የኤርትራን ጸጥታ ከዳር እስከ ዳር በአብዛኛው የሚጠብቀው የኤርትራ ፖሊስ ሠራዊትና ፈጥኖ ደራሽ ኮማንዲስ ፖሊስ ነበር። ፈጥኖ ደራሹም ሆነ ፖሊስ ሠራዊቱ 90% በላይ የኤርትራ ተወላጆች ነበሩ ። የኤርትራን ባሕር በር ጉምሩክ ፤ የፋይናንስ ፤ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችንና ሌሎቹም ሁሉ የሚጠብቁ የኤርትራ ተወላጆች ነበሩ። ጃንሆይ በደርግ ተይዘው እስከ ተገደሉበት እስከ 1966 ዓም ድረስ በእየ ዓመቱ ከአሥመራ ምፅዋ የሚሄዱትና የሚዘዋወሩት በመኪና እንጂ በሄሊኮፕተር ውይም በአይሮፕላን አልነበረም። በእርግጥ ግን አልፎ አልፎ የወንበዴዎች ችግር መኖሩ አይካድም።

በአዲስ አበባ እና በአሠመራ የነበረውን የኢትዮጵያ ሥርአት እና የመንግሥት አቋም ደርግ ሲያናጋው ፤ ብዙ አረጋዊያን ኤርትራዊያን ተደናግጠዋል። በኤርትራ እያንዳንዱ አውራጃ የራሱ ልዩ የሆነ መልክና ጠባይ አለው። መሪዎቹን ደጃዝማቾችን ፤ ራሦችን፤ ቄሶችን ፤ ሼኮችን ፤ ከራሱ ስለሆኑ ፤ የተሾሙ ሹሞችን ያምናል ይቀበላል። ይህንን ንጉሠ ነገሥቱ አምነው ተቀብለውት ነበር። አዎ ወጣቱ ትውልድ በኤርትራ ብቻ ሳይሆን በሌላውም የኢትዮጵያ ግዛት አብዮት አወናብዶት እንደነበረ ይታወሳል። እንደሚታወቀው ኤርትራ ከኢትዮጵያ የተዋሀደችው ፤ በጦር ኃይል ሳይሆን ፤ በሀገር ወዳድ ኤርትራዊያን አንድነትና ሀገር ፍቅር ጥንካሬ በፓርላማ ምርጫ ነው። በእየትኛው ም ዓለም ቢሆን ምርጫ ፍጹም አይደለም። ደጋፊና ተቃዋሚ ይኖረዋል። አንዳንድ ፀረ እንድነቶች እና የኢትዮጵያ ጠላቶች ሀሰትን ሲያራግቡት ይኖራሉ። በሌላ በኩልም ብናየው በፈደሬሽንም ቢሆን ኢትዮጵያና ኤርትሪያ አይነጣጠሉም ነበር ።

እኔ ለብዙ ዓመታት በኤርትራ በነበርኩበት ጊዜ በእድሜ በሰል ያሉ አረጋዊያን የኢጣሊያን እና የእንግሊዝን የጭቆና አገዛዝ የሚያውቁና የሚያስታውሱ ኢትዮጵያን ያፈቅሩ ነበር። ነገር ግን በአረቦች ግፊት በተለይ በገብፅ ፤ ሲሪያ ፤ ኢራቅ ፤ ሱዳን

ገንዘብና እርዳታ አረባዊ የሆኑ ፤ በቅድሚያ ጀብሃት ቀጥሎም ሸአቢያ የተባሉ የአረብ ስምና አሠላለፍ ተቀብሎ ወጣቱ ወነበደ። በዚያኑ ዘመን ሶቪየት ዩንየንም ሶሺያሊዝምን በ P L O እና በባዓዝ ፓርቲ አማካይነት የጦር መሣሪያና ገንዘብ በመለገስ በእነዚህ የኤርትራ ድርጅቶች ውስጥ ፀረ ኢትዮጵያና ፀረ አሜሪካ አብዮት ማስፋፋት ቀጠለ ።

ይሁን እንጂ ደርግ የኢትዮጵያን መንግሥት ከመያዙ በፊት የጀብሃት ተዋጊዮች አልፎ አልፎ አደጋ ከመጣል በስተቀር አንድ መንደር እንኳን አልያዙም ነበር። ሺአቢያ የተባለው አሁን ኤርትሪያን የሚያስተዳድረው ቡድን በሃማሴን አውራጃ ብቻ የሚንቀሳቀስ ነበር። ነገር ግን ደርግ ከተፈጠረ በኋላ የአዲስ አበባን መንግሥት ንዶ በኤርትራ የነበሩትን ሹማምንት እና መሪዮች መያዝና ማሠር ብሎም መግደል ሲጀምር ፤ ገመዱ እንደተበጠሰ ጭነት የኤርትራ ጉዳይ ብትንትኑ ወጣ ።

ይህ በዚህ ላይ እንዳለ ፤ ጀኔራል አማን ኤርትራ መጥተው በሁሉም ከተማዎችና ካምፖች እየተዘዋወሩ ትምህርትና ከፍተኛ ማስጠንቀቂያ አቅርበዋል። ህዝቡ በደስታ ሲቀበላቸው ወንበዴዎቹ በጣም ተደናግጠው ነበር ። በዚህ ጊዜ ጀኔራል አማን በኢትዮጵያ ጦርና መንግሥት የሚተማመኑ ሰው ስለነበሩ ተስፋ አድርገው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ ።

አዲስ አበባ እንደደረሱ ሥልጣን ፈላጊዎቹ ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይላማሪያም እና ሌ/ኮሎኔል አጥናፉ አባት የጀኔራሉን መግነንና በህዝብ ተወዳጅነት አልወደዱም ፤ ቀስ በቀስ ሀሰት ያስወሩባቸው ጀመር ።ቀጥሎም ምክራቸውንና ትእዛዛቸውን መቀበል አቆሙ። እዚህ ላይ እናስታውስ ደርግ በእንጭጭነቱ ወቀት የደርግ አባላት ሲፈሩና ሲርበተበቱ መከታቸው ጀኔራል አማን ነበሩ። የኃይለ ሥላሴን መንግሥት ሲገለብጡ ብዙዎቹ ፈርተው በነበሩበት ወቅት ለውሣኔ የደረሱት ጀነራል አማንን መከታ አድርገው ነበር። ያ ሁሉ አልፎ ከተጠቀሙባቸው በኋል ምክንያት ፈልገው በ NOV 23 1974 ( 1966 በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ) ገደሏቸው። ከዚህ በኋላ የኤርትራ ጉዳይ አብሯቸው ሞተ ።

በመሰረቱ ጀነራል አማን አንዶም እና ጀነራል ተፈሪ በንቲ ከደርግ ጋር መስራት በፍጹም አልነበረባቸውም ።

ጀነራል ጎይቶም በኤሊባቦርና በኤርትራ የፖሊስ ሠራዊት አዛዥ ሆነው ሠርተዋል። ጀነራል ጎይቶም የሠራዬ ተወላጅ ፤ ኢትዮጵያ ወይም ሞት ያሉና ለኢትዮጵያ አንድነት የታገሉ የሀገር ፍቅር አባል እና መስራች ኢትዮጵያዊ ነበሩ ። በኤርትራ ውስጥ ከጀበሀት ጥይት የተረፉትን ኤርትራዊያን ሹማምንት ወንድሞቻቸውንና የአንድነት ፓርቲ አባላትን ፤ ደርግ ያላንዳች ምክንያት አድሃሪ እያለ በማሠሩ በማንገላታቱ እና በመግደሉ በጣም ቅር ተሰኝተው፤ ይህ ጉዳይ አግባብ ባለመሆኑ ህዝቡ ስለተከፋ እንዲቆ ም ለደርግ አሳሰቡ ። እንዲያውም ከጥቂት ጊዜ በኋል ጀነራል ጎይቶምን ለማሠር ከደርግ ተእዛዝ መተላለፉ እንደደረሳቸው ህይወታቸውን ለማዳን ከደርግ ሸሽተው ከአገር ወጥተዋ ል ። ጀነራል ጎይቶም የፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ አዛዥ ሳይሆኑ የኤርትራ ፖሊስ ሠራዊት አዛዥ ነበሩ። ፈጥኖ ደራሽ ፖሊሶችን ሰብስበው በረሃ አልገቡም። ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ አሁን ም ተሳስቷል። ነገር ግን ጀኔራል አማን ከተገደሉ በኋላ በደርግ ውሣኔ ተበሳጭቶ ሻምበል ሚካኤል ገብረንጉሥ የኤርትራ ፖሊስ የደርግ አባል ሕግ አዋቂ ኮብልሎ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ሸአቢያን ተቀላቅሏል።

ጀግናው የኤርትራ ፈጥኖ ደራሽ ፖሊስ ሠራዊት በኤርት ራ ኮማንዲስ ተበሎ የሚታወቀው ሊፈርስ የቻለው ፤ ደርግ ሆን ብሎ ባደረገው የአመራር ዝርክርክነት ነው። ከዚህም በተጨማሪ ተደጋግሞ በደረሰበት ጭቆናና አድልዎ እንዲሁም ያለመተማመን ነው እንጂ ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ እንዳለው አይደለም።

ለማጠቃለል ያህል ፤ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ አለቃው እና አስተማሪው የነበሩትን ኮሎኔል ካሣ ገብረማሪያምን ማስገደል ብቻ ሳይሆን ፤ ንጉሡንና ንጉሣዊ ቤተሰቦችን ፤ አርበኞችን፤ ባለስላጣናትን፤ ፓትሪያርክን፤ ጀኔራሎችን፤ መኮንኖችንና ወታደሮችን፤ አዛውንቶችን ፤ ሴቶችን ፤ወጣቶችን፤ ምሁሮችን፤ ተማሪዎችን፤ ገበሬዎችን ፤ ወዝ አደሮችን፤ ሠፋሪዎችን ___ወዘተ ገድሏል አስገድሏል። ይህ የማይታበል ሀቅ ነው። ጥበብና አስተዋይነት የጎደለው የደርግ ፋሺሽታዊ አመራር የኢትዮጵያን ህዝብ ብቻ ሳይሆን የጎዳው፤ ኢትዮጵያም ህልውናዋ እንዲዳከምና ኤርትራ እንድትገነጠል ረድቷል። ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ በህዝብ ላይ ለፈጸማቸው ወንጀሎች ለፍርድ መቅረብ ሲገባው፤ በዘረፈው ገንዘብ በስደት እየተዝናና ይገኛል። በዚህ ሰው ላይ ምንም እርምጃ ባለመውሰዳችን ፤ መጭው ትውልድና ታሪክ ሲያዝንብን ይኖራል።በአባቶቻቸው ፤ በእናቶቻቸው፤ በጓደኞቻቸው በጠቅላላው ኢትዮጵያዊያን ወገኖቻችን ላይ የተፈጸሙትን በደሎች የሚያሳዩ አያሌ መጽሐፎች ተጽፈው አንብበናል ። ወደ ፊትም ሌሎች ብዙዎች ተጽፈው ለሕዝብ ይቀርባሉ። ነገር ግን የእነዚህ ሁሉ እንባና ድካም ውጤት የሚኖረው ሌ/ኮሎኔል መንግሥቱ ለፍርድ ሲቀርብ ብቻ ነው።

ሻምበል ግዛው ገድሉ